# መዝሙር ፡ ፹፯ ።

፩ ፡ እግዚ.አብሔር ፡ አምላኪ፡መድኃኒትየ

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ታናግሮታል ፤ እግዚ. አብሔር ፡ ድኅነቴን፡የሚያደርግልኝ፡ ፈጣሪዬ ፡ ነው ፤ ፈጣሪዬ ፡ እግዚ.አብ ሔር ፡ ድኅነቴን ፡ የሚያደርግልኝ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ ሰሚ ፡ አድርገህ ፡ ድ ኅነቴን ፡ የምታደርግልኝ ፡ ፈጣሪዬ ፡ እግዚ.አብሔር ። ኢሳ ፡ ፲፱ ።

ዕለትየ ፡ ጸራኅኩ ፡ ኀቤከ ፡ ወሌሊትየኒ ፡ ቅ ድ ሜ ከ ።

ለኔ ፡ ብለህ ፡ በፈጠርህልኝ፡ ሌሊትና፡ መዓልት ፡ ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ ለመ ንኁ ፤ መዓልትና፡ ሌሊት ፡ መፈጠሩ ፡ ለሰው ፡ ነውና ፤ ወበእንቲአክሙ ፡ ፈ ጠርክዋ፡ ለዕለት ፡ እንዲል ፤ አንድም፡ ለምኖለኅና ፤ ኢሳ ፡ ፷፯ ፡ ፱ ።

፪ ፡ ለትባዕ ፡ ጸሎትየ ፡ ቅድሜከ ።

ልመናዬ ፡ ከፊትህ ፡ ትድረስ ።

አፅምዕ ፡ ዕዝነከ ፡ ኀበ ፡ ስእለትየ ።

ዕዝነ፡ምሕረትህን ፤ ዕዝነ፡ፈቃድህን፡ ወደ ፡ ልመናዬን ፡ መልሰህ ፡ ስማኝ ።

፫ ፡ እስመ ፡ ጸግበት ፡ ነፍስየ ፡ ሕማመ።

ሰውነቴ ፡ መከራውን፡ሰልችታለችና ፤

ወአልጸቀት ፡ ለሞት ፡ ሕይወትየ ።

ሰውነቴ ፡ ለሞት ፡ ደርሳለችና ።

፬ ፡ ወተኈለቁ ፡ ከመ ፡ እለ ፡ ይወርዱ ፡ ውስተ ፡ ዐዘቅት ።

ሙተው ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ከወረዱ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ተቈጠርኍ ፤ አንድም ፡ ሙተው ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ እንደ ፡ ወረዱ ፡ ሰዎች ፡ ሆንሁ ፡ ሐዲስ ፡ እን ዳለፈው ።

ወኮንኩ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ዘአልቦ፡ረዳኢ.

ረዳት ፡ እንደ ፡ ሌለው ፡ ሰው ፡ ሆንኍ ፤ አንድም ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ አደረጉኝ ።

፭ ፡ ግዑዘ ፡ ውስተ ፡ ምዉታን ።

ጉዞዬንም ፡ ወደ ፡ ምውታን ፡ አቃና ኍ ፡ አደረግኍ ፤ አንድም ፡ (ግዑዝ) ፡ ጉዞዬ ፡ ከሙታን ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ ኸነ ፤ አንድም ፡ (እንዘ ፡ ግዑዝ) ፡ በመለኮቴ ፡ ከሕማም ፡ ከሞት ፡ ግዑዝ ፡ ስሆን ፡ ከሙታን ፡ ጋራ ፡ ተቈጠርኍ ፤ አን ድም ፡ ከሙታን ፡ ጋራ ፡ ከተቈጠርኍ ፡ በኋላ ፡ በትንሣኤ ፡ ግዑዝ ፡ ነኝ ።

ከመ ፡ ቅቱላን ፡ ወግዱፋን ፡ እለ ፡ ይስ ክቡ ፡ ውስተ ፡ መቃብር ።

ሙተው ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ እንደ ፡ ተጣሉ ፡ ሰዎች ፡ ሆንሁ ፤ አንድም ፡ ሙተው ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ከወረዱ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ተቈጠርኍ ፤ ኢዮ ፡ ፲፯ ፡ ፲፫ ።

እለ ፡ ኢዘከርኮሙ ፡ ለግሙራ ።

ፈጽመህ ፡ ልብስ ፡ ምግብ ፡ ዝናብ ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ እንዳላልሃቸ ው ፡ ሰዎች ።

እስመ ፡ እሙንቱሂ ፡ ርኁቁ ፡ እምእዴከ ኢሳ ፡ ፲ ፡ ፬ ።

እነዚህም ፡ ከዕደ ፡ ምሕረትህ ፡ ፈጽ መው ፡ ርቀዋልና ።

ወጽድቀከኒ ፡ በማኅበረ ፡ ቅዱሳን ።

ቸርነትህም ፡ በመላእክት ፡ ዘንድ ፤ እንድም ፡ በነቢያት ፡ በካህናት ፡ ጉባዔ ፡ ይነገራል ፡ ይመሰገናል ።

፮ ፡ መኑ ፤ ይትዔረዮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በደመናት ።

እግዚአብሔርን ፡ ደመናትን ፡ በመፍጠር ፡ አንድም ፡ በልዕልና ፡ አንድም ፡ ሥጋን ፡ ነፍስን ፡ ፈጥሮ ፡ በማዋሀድ ፡ የሚመስለው ፤ (የሚተካከለው ፡ ማን ፡ ነው ኢሳ ፡ ፵፮ ፡ ፭ ።

ወመኑ ፡ ይመስሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እምደቂቀ ፡ አማልክት ።

በስመ ፡ አማልክት ፡ ከሚጠሩ ፡ አማልክት ፡ ነን ፡ ከሚሉስ ፡ ወገን ፡ የሚመስለው ፡ ማን ፡ ነው ።

፯ ፤ እግዚአብሔር ፡ ስቡሕ ፡ በምክረ ፡ ቅዱሳን ።

እግዚአብሔር ፡ በመላእክት ፡ ቃል ፡ አንድም ፡ በነቢያት ፡ በካህናት ፡ ቃል ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ።

ዐቢይ ፡ ወግሩም ፡ ዲበ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ዐውዱ ።

በመንበረ ፡ መንግሥቱ ፡ ዙርያ ፡ ባሉ ፡ በሱራፌል ፡ በኪሩቤል ፡ ላይ ፡ አንድም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ዙርያ ፡ ባሉ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ግሩም ፡ ነው ፤ ገናና ፡ አምላክ ፡ ነው ።

፰ ፤ እግዚኦ ፡ አምላከ ፡ ኃያላን ፡ መኑ ከማከ ።

አቤቱ ፡ የኃያላኑ ፡ ባለቤት ፡ ማዳን ፡ መታደግ ፡ የሚቻለው ፡ እንዳንተ ፡ ያለ ፡ ማን ፡ ነው ።

ኃያል ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ወጽድቅ ፡ የዐውደከ ።

አቤቱ ፡ ኃያል ፡ ነህ ፡ ላጥፋ ፡ ብትል ፡ ይቻልሃል ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ ቸርነትህ ፡ ይገላግልሃል ።

፱ ፤ አንተ ፡ ትኴንን ፡ ኃይለ ፡ ባሕር ።

ውቅያኖስን ፡ የምትገዛ ፡ አንተ ፡ ነህ ።

ወአንተ ፡ ታረምሞ ፡ ለድምፀ ፡ ማዕበሉ

እስከ ፡ ዝየ ፡ ብጽሒ ፡ ብለህ ፡ የውቅያኖስን ፡ ማዕበል ፡ ሞገዱን ፡ ፀጥ ፡ የምታደርገው ፡ አንተ ፡ ነህ ።

፲ ፤ አንተ ፡ አኅሠርኮ ፡ ለዕቡይ ፡ ከመ ፡ ቅቱል ። ፶፩ ፡ ፶፩ ፡ ፱ ፡ ፲ ።

ሌዋታንን ፡ እንደሞተ ፡ ያዋረድከው ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ማለት ፡ በባሕር ፡ ተወስኖ ፡ እንዲኖር ፡ ያደረግኸው ።

ወበመዝራዕተ ፡ ኃይልከ ፡ ዘረውኮሙ ፡ ለጸርከ ።

ኃይል ፡ ባለው ፡ ሥልጣንህም ፡ አጋንንትን ፡ በየቦታቸው ፡ ወሰንሃቸው ፥ በአየር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በአንጦርጦስ ፤ አንድም ፡ ግሩማን ፡ አራዊትን ፡ በየቦታቸው ፡ ወሰንሃቸው ።

አንድም ፡ (አንተ ፡ ትኴንን) ፡ ኤርትራን ፡ የምትገዛ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (ወአንተ) ፡ የኤርትራን ፡ ማዕበል ፡ ሞገዱን ፡ ከሁለት ፡ ከሦስት ፡ ከፍለህ ፡ ፀጥ ፡ ያደረግኸው ፡ አንተ ፡ ነህ ፥ (አንተ ፡ አኅሠርኮ) ፡ ፈርዖንን ፡ በኤርትራ ፡ ሠጥሞ ፡ እንዲቀር ፡ ያደረግኸው ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (ወበመዝራዕተ) ፡ ሠራዊተ ፡ ፈር

ያንንም ፡ ከሥልጣንህ ፡ በተገኘ ፡ ኃይልህ ፡ ያጠፋሃቸው ፡ አንተ ፡ ነህ ።

አንድም ፡ አንተ ፡ (ትኴንን) ፡ ባቢሎንን ፡ የምትገዛ ፡ አንተ ፡ ነህ ፥ (ወአንተ ፡ ታረምሞ) ፡ የባቢሎንን ፡ የመከራዋን ፡ ፅናት ፡ ፀጥ ፡ ያደረግሽው ፡ ያጠፋሽው ፡ አንተ ፡ ነህ ።(አንተ ፡ አኅሠርኮ) ፡ ብልጣሶርን ፡ በከተማው ፡ ቸብቸበው ፡ ተቈርጦ ፡ እንዲቀር ፡ ያደረግሽው ፡ አንተ ፡ ነህ ፥ (ወበመዝራዕተ ፡ ኃይልከ) ፡ ከሥልጣንህ ፡ በተገኘ ፡ ኃይልህ ፡ ሠራዊተ ፡ ብልጣሶርን ፡ አጠፋኻቸው ። አንድም ፡ (አንተ ፡ ትኴንን) ፡ ገሃነምን ፡ የምትገዛ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (ወንንተ ፡ ታረምሞ) ፡ የገሃነምን ፡ የመከራዋን ፡ ፅናት ፡ ፀጥ ፡ ያደረግሽው ፡ ያጠፋሽው ፡ አንተ ፡ ነህ ፥ (አንተ ፡ አኅሠርኮ) ፡ ዲያብሎስን ፡ በጥምቀት ፡ በመስቀል ፡ ድል ፡ የነሳሽው ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ (ወበመዝራዕተ ፡ ኃይልከ) ፡ ሠራዊተ ፡ ዲያብሎስን ፡ አጋንንትን ፡ አጠፋሃቸው ።

**፲፩ ፡ ዚአከ ፡ ውእቱ ፡ ሰማያት ፡ ወእንቲአከ ፡ ይእቲ ፡ ምድር ።**

ሰማዮች ፡ ያንተ ፡ ገንዘቦች ፡ ናቸው ፤ ምድርም ፡ ያንተ ፡ ገንዘብ ፡ ናት ።

**ዓለመኒ ፡ በምልኡ ፡ አንተ ፡ ሣረርከ ።**

ዓለምንም ፡ በሙሉ ፡ በጥቅልሉ ፡ አንተ ፡ ፈጠርህ ፤ አንድም ፡ የፈጠርህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ መዝ ፡ ፹፱ ፡ ፩-፪ ።

**፲፪ ፡ ባሕረ ፡ ወመስዐ ፡ ዘአንተ ፡ ፈጠርከ**

ባሕሩን ፡ የብሱን ፡ የፈጠርህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ አንድም ፡ ንዑሳን ፡ መዓዝን ፡ የመዓዝን ፡ መዓዝን ፡ አሉና ፥ እነያን ፡ የፈጠርህ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ ባርክ ፡ ምሥራቀ ፡ ወምዕራበ ፥ ሰሜነ ፡ ወደቡበ ፥ መሥዓ ፡ ወዓዜበ ፥ ሊበ ፡ ወባሕረ ፡ እንዲል ።

**ታቦር ፡ ወአርሞንኤም ፡ በስመ ፡ ዚአከ ይትፌሥሑ ።**

ታቦርና ፡ አርሞንኤም ፡ በስምህ ፡ አምነው ፡ በተደረገላቸው ፡ ነገር ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፤ በገሪቱ ፡ ሰዎቹን ፡ መናገር ፡ ነው ፥ ባርቅ ፡ ሲሣራን ፡ ድል ፡ አድርጎበታልና ፥ ምነው ፡ ይህማ ፡ የተደረገው ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ አይደለምን ፥ አርሞንኤምን ፡ አነሣ ፡ ቢሉ ፥ አባራፊው ፡ እስከ ፡ አርሞንኤም ፡ ደርሷልና ።

**ወይሴብሑ ፡ ለስምከ ።**

ስምህን ፡ ያመሰግናሉ ፥ ለስምህ ፡ ምስጋና ፡ ያቀርባሉ ።

**፲፫ ፡ መዝራዕትከ ፡ ምስለ ፡ ኃይል ።**

ሥልጣንህ ፡ ከኃይል ፡ ጋራ ፡ ተደረገላቸው ፤ አንድም ፡ (ታቦር ፡ ወአርሞንኤም) ፡ ሐዋርያት ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ በአርሞንኤም ፡ ብርሃን ፡ መለኮትህን ፡ ዓይተው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፥ ምነው ፡ ይህማ ፡ የተደረገው ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ አይደለምን ፡ አርሞንኤምን ፡ አነሣ ፡ ቢሉ ፡ ብርሃኑ ፡ እስከ ፡ አርሞንኤም ፡

ወትቤ ፡ እሬሲ ፡ ረድኤተ፡በላዕለ፡ኃይል

ረድኤትን ፡ በኃይል ፡ ላይ ፡ አደር ጋለሁ ፡ ማለት ፡ በሠራዊቱ ፡ ኃይ ልን ፡ አደርጋለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወአልዐልኩ ፡ ኅሩየ ፡ እምሕዝብየ ።

አልዓልኩ ፡ እምሕዝብየ ፡ ኅሩይየ ፡ እምሕዝብየ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ ለመ ንግሥት ፡ የመረጥሁት ፡ ዳዊትን ፡ በመንግሥት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደርገ ዋለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ፡ አንድም ፡ ዳዊትን ፡ ከወገኖቼ ፡ ለይቼ ፡ በመ ንግሥት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደርገዋ ለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፳ ፡ ወረከብክዎ ፡ ለዳዊት ፡ ገብርየ ።

አገልጋዬ ፡ ባለሟሌ ፡ ዳዊትን ፡ ለመንግሥት ፡ የበቃ ፡ ሁኖ ፡ አገ ኘሁት ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወቀባዕክዎ ፡ ቅብዐ ፡ ቅዱስ ።

ልዩ፡ ቅብዕን ፡ ቀብቼ ፡ አነገሥሁት፡ ብለህ ፡ ነበር ፡ ክብሩን ፡ ሲያይ ፡ ነው፡ እንጂ ፡ ቅብውስ፡ አንድ፡ ነው ።

፳፩ ፡ እስመ ፡ እዴየ ፡ ትረድኦ ።

ኃይሌ ፡ ትረዳዋለች ፡ ብለህ ፡ ነበር።

ወመዝራዕትየ ፡ ታጸንዖ ። ኢሳ ፡ ፷፩ ፡ ፲።

ሥልጣኔ ፡ ታፀናዋለች ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፳፪ ፡ ወኢይበቊዕ ፡ ጸላዒ ፡ በላዕሌሁ ።

ጠላት ፡ በሱ ፡ አይሰለጥንበትም ፡ አንድም ፡ በሱ ፡ የሚነሣ ፡ ጠላት ፡ አይረባም ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወውሉደ ፡ ዐመፃ ፡ ኢይደግም ፡ አሕምሞቶ ።

የዓመፅ ፡ ልጅ ፡ ባቢሎናዊ ፡ በሱ ፡ መከራ ፡ ማምጣትን ፡ አይደግምም፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ቢነሣበት ፡ እንደ ፡ ተነሣበት ፡ አይቀርም ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፳፫ ፡ ወእመትሮሙ ፡ ለጸሩ ፡ እምቅድመ ገጹ ።

በቅድመ ፡ ገጹ ፡ ይላል ፡ ጠላቶ ቹን ፡ ከፊቱ ፡ አንድም ፡ በፊቱ ፡ አጠፋቸዋለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወአኃሥሮሙ ፡ ለጸላዕቱ ።

ጠላቶቹን ፡ አጠፋቸዋለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ። ኢሳ ፡ ፲፫ ፡ ፲፩ ።

፳፬ ፡ ወማሀልየሰ ፡ ወጽድቅየ ፡ ምስሌሁ

ሎቱሰ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ ለሱ ፡ ግን ፡ ይቅርታዬን ፡ ቸርነቴን ፡ አደር ግለታለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወበስምየ ፡ ይትሌዐል ፡ ቀርኑ ።

በስሜ ፡ አምኖ ፡ ሥልጣኑ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፳፭ ፡ ወእሠይም ፡ ውስተ፡ባሕር፡እዴሁ

ግዛቱን ፡ ከጤግሮስ ፡ እስከ ፡ ኤፍ ራጥስ ፡ አደርገዋለሁ ፡ ይገዛል ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወውስተ ፡ አፍላግ ፡ የማኖ ።

ሥልጣኑንም ፡ ከዳን ፡ እስከ ፡ ቤር

ሳቤህ ፡ አደርገዋለሁ ፡ ይገዛል ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፳፮ ፡ ወውእቱ ፡ ይብለኒ ፡ አቡየ ፡ አንተ

ዳዊት ፡ በጸጋ ፡ አባቴ ፡ ነው ፡ ይለኛል ፡ እኔም ፡ ልጄ ፡ ነው ፡ እለዋለሁ ፡ አንድም ፡ ክርስቶስ ፡ በባሕርይ ፡ አባቴ ፡ ነው ፡ ይለኛል ፡ እኔም ፡ ልጄ ፡ ነው ፡ እለዋለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ፡ መዝ ፡ ፪ ፡ ፯ ፡፡ ፪ ፡ ነገ ፡ ፯ ፡ ፲፬

አምላኪየ ፡ ረዳኢየ ፡ ወመድኃኒየ ፡ ዕብ ፡ ፩ ፡ ፭ ።

ድኅነቴን ፡ የምታደርግልኝ ፡ ረዳቴ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ነህ ፡ ይለኛል ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፳፯ ፡ ወአነኒ ፡ በኵርየ ፡ እሬስዮ ።

እኔም ፡ በኵረ ፡ ምዕመናን ፡ በኵረ ፡ ነገሥታት ፡ አደርገዋለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወልዑል ፡ ውእቱ ፡ እምነገሥተ ፡ ምድር

በእሬስዮ ፡ የሣብህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ልዑለ ፡ በውእቱ ፡ የሣብህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ልዑል ፡ በል ፡ በአራቱ ፡ መዓዝን ፡ ከነገሡ ፡ ነገሥታት ፡ ይልቅ ፡ ልዑል ፡ ንጉሥ ፡ አደርገዋለሁ ፡ አንድም ፡ ልዑል ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፳፰ ፡ ወለዓለም ፡ አዐቅብ ፡ ሎቱ ፡ ሣህልየ

ለሱ ፡ ለዘላለም ፡ ይቅርታዬን ፡ መሐላዬን ፡ አፀናለታለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወምእመን ፡ ውእቱ ፡ ለኪዳንየ ።

ሕጌን ፡ ለመጠበቅ ፡ የታመነ ፡ ነው ፡ ሊምሉለት ፡ ይገባል ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፳፱ ፡ ወእሬሲ ፡ ዘርዖ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

ልጆቹን ፡ ለዘላለም ፡ በመንግሥት ፡ የተዘጋጁ ፡ አደርጋቸዋለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወመንበሩሂ ፡ ከመ ፡ መዋዕለ ፡ ሰማይ ።

መንበረ ፡ መንግሥቱም ፡ ሰማይ ፡ ሳያልፍ ፡ አያልፍም ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

፪ ፡ ነገ ፡ ፯ ፡ ፲፪ ። ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ።
፴ ፡ እመሰ ፡ ኀደጉ ፡ ደቂቁ ፡ ሕግየ ።

ልጆቹ ፡ ግን ፡ ሕጌን ፡ ቢያፈርሱ ፡

ወኢሖሩ ፡ በኵነኔየ ።

በሕጌም ፡ ፀንተው ፡ ባይኖሩ ፡

፴፩ ፡ ወእመሂ ፡ አርኰሱ ፡ ሥርዓትየ ።

ሕጌንም ፡ ቢያፈርሱ ፡

ወኢዐቀቡ ፡ ትእዛዝየ ።

ሕጌንም ፡ ባይጠብቁ ፡

፴፪ ፡ አዋግዮ ፡ በበትር ፡ ለኃጢአቶሙ ።

በታናሽ ፡ መቅሠፍት ፡ እገሥጻቸዋለሁ ፡ ብለህ ፡ ነበር ።

ወበመቅሠፍት ፡ ለአበሳሆሙ ።

ልጅ ፡ ቢያጠፋ ፡ በጨንገር ፡ ይሠሩታል ፡ ይቀጡታል ፡ እንጂ ፡ በሰይፍ ፡ እንዳይመቱት ፡ በጦር ፡ እን

ዘመሐልከ ፡ ለዳዊት ፡ ገብርከ ፡ በጽድቅ

ላገልጋይህ ፡ ለዳዊት ፡ በውነት ፡ የማልከው ፡ መሐላ ፡ ወዴት ፡ አለ ።

፶ ፡ ተዘከር ፡ እግዚኦ ፡ ዘጸዐልዎሙ ፡ ለአግብርቲከ ።

አቤቱ ፡ ባሮችህ ፡ ትሩፋንን ፡ የሰደቡአቸውን ፡ ስድብ ፡ አንድም ፡ የሚሳደቡ ፡ አሕዛብን ፡ አስብ ፡ አስበሕ ፡ አውጣን ።

ዘተወከፍኩ ፡ በሕፅንየ ፡ ብዙኃ ፡ አሕዛብ

በክንዴ ፡ የተሸከምኋቸው ፡ ብዙ ፡ አሕዛብን ፡ አስብ ፡ አስበህ ፡ አውጣን ፡ የተሸከምኋቸውን ፡ መሸከም ፡ አለ ፡ ድንኂ፡ ወንትዐዶ፡ ብኪ፡ እያሉ ፡ ኮር ፡ ይወጡባቸዋል ፡ ፈረፈር ፡ ይሻገሩባቸዋል ፡ የመሸታ ፡ ጠላ ፡ ይቀዱባቸዋልና ።

፶፩ ፡ ዘጸዐሉ ፡ ጸላዕትከ ፡ እግዚኦ ።

ጠላቶችህ ፡ ባቢሎናውያን ፡ የሚሳደቡትን ፡ ስድብ ፡ አስብ ፡ አንድም ፡ ጸላዕተከ ፡ የሚሳደቡ ፡ ጠላቶችህ ፡ ባቢሎናውያንን ፡ አስብ ፡ አስበህ ፡ አውጣን ።

ወጸዐሉ ፡ ዕቤራተ ፡ መሢሕከ ።

ቀብተህ ፡ ያነገሥሀቸው ፡ የነገሥታቱን ፡ እናት ፡ የሚሳደቡ ፡ ባቢሎናውያንን ፡ አስብ ፡ ማርከው ፡ ወስደው ፡ ሞግዚት ፡ ደንገ ፡ ጡር ፡ ገረድ ፡ አበዛ ፡ ጋጋሪ ፡ ያደርጓቸዋል ፡ ያለመዱት ፡ ነውና ፡ አይሆንላቸውም ፡ ስለዚህ ፡ ሴትነታቸው ፡ ነውን ፡ ይሏቸዋልና ፡ አንድም ፡ ያለ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ይደርሱባቸዋል ፡ ስለዚህ ፡ ሴትነታቸው ፡ ምን ፡ ያጓድዳቸዋል ፡ ብለው ፡ ይሰድቧቸዋልና ፡ አንድም ፡ ዕብሬተ ፡ መሲሕከ ፡ ነገሥታቱ ፡ የነገሡባቸውን ፡ ዘመናት ፡ የሚሳደቡ ፡ ባቢሎናውውያንን ፡ አስብ ፡ የዮአክስ ፡ የኢኮንያን ፡ መንግሥት ፡ የሦስት ፡ ወር ፡ መንግሥት ፡ ከመንግሥት ፡ ሊቈጠር ፡ ነውን ፡ እያሉ ።

፶፪ ፡ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዓለም ለይኩን ፡ ለይኩን ።

እግዚአብሔር ፡ ለዘላለሙ ፡ ይክበር፡ ይመስገን ፡ ይኹውም ፡ ይደረግ ፡ ይደረግ ፡ መከራውን ፡ ተናግሮ ፡ ይትባረክ ፡ አለ ፡ ይሙት ፡ በቃ ፡ የተፈረደበት ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ እንዲሄድ ፡ እስከዚህ ፡ በሦስት ፡ ለይኩን ፡ ከፍሎ ፡ ተናግሮታል ።

## መዝሙር ፡ ፹፱ ።

፩ ፡ እግዚኦ ፡ ፀወነ ፡ ኮንከነ ፡ ለትውልደ ትውልድ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ አቤቱ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ አምባ ፡ መፀግያ ፡ ሆንኸን ።

፯ ፤ እስመ ፡ ኅለቅነ ፡ በመዓትከ ።

በመዓትህ ፡ ተፈጽመናልና ፡ ይወድቅ ፡ አንድም ፡ እንዲህ ፡ ነውና ።

ወደንገፅነ ፡ በመቅሠፍትከ ።

በመቅሠፍትህ ፡ ደነገጥን ።

፰ ፤ ወሤምከ ፡ ኃጢአተነ ፡ ቅድሜከ ።

ኃጢአታችንን ፡ በፊትህ ፡ አኖርህ ፡ ማለት ፡ ታውቀዋለህ ፡ አንድም ፡ ታውቀዋለህና ፡ ።

ወዓለምነሂ ፡ ውስተ ፡ ብርሃነ ፡ ገጽከ ።

ደስ ፡ ብሎን ፡ የሠራነውን ፡ ኃጢአታችንን ፡ ታውቀዋለህ ፡ አንድም ፡ ትሩፍ ፡ ዓለመኛ ፡ ነህና ፡ መከራ ፡ አይንካኝ ፡ ትል ፡ እንጂ ፡ ይሆናል ፡ ትለኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የኛስ ፡ ተድላችን ፡ የፊትህ ፡ ብርሃን ፡ ተሥሎበት ፡ በተወለደ ፡ በሙሴ ፡ ጊዜ ፡ ቀርቷል ።

፱ ፡ እስመ ፡ ኅልቃ ፡ ኵሎን ፡ መዋዕሊነ።

ዘመናችን ፡ በመከራው ፡ ተፈጽሟልና፡ ወዓለምነሂ ። አንድም ፡ እንዲህ፡ በመከራው ፡ ተፈጽሟልና ።

ወኀለቅነ ፡ በመቅሠፍትከ ።

በመቅሠፍትህ ፡ ተፈጸምን።

፲ ፡ ወዓመቲነሂ ፡ ከመ ፡ ሣሬት ፡ ይከውና

ዘመኖቻችንም ፡ እንደ ፡ ሸረሪት ፡ ይሆናሉ ፡ ማለት ፡ ሸረሪት ፡ ከእሳት ፡ የገባች ፡ እንደሆነ ፡ አጥንት ፡ ጉልጥምት ፡ የላትም ፡ ቀልጣ ፡ ትጠፋለች ፡ ሰውም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ ደረሰ ፡ አይባልምና ።

ወመዋዕለ ፡ ዓመቲነኒ ፡ ፸ ፡ ክራማት ።

ትሩፋን ፡ በባቢሎን ፡ የሚኖሩት ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ነው ።

ወእመሰ ፡ በዝኅ ፡ ሰማኒያ ፡ ዓም ። ሚራ ፡ ፲፰ ፡ ፱—፲ ።

ከዚያም ፡ ዕልፍ ፡ ቢል ፡ ሰማንያ፡ ዘመን ፡ ነው ።

ወፈድፋዶንሰ ፡ እምእላ፡ ፃማ ፡ ወሕማም

ከዚህ ፡ ከሰማንያ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በባቢሎናውያን ፡ ዘንድ ፡ ጻር ፡ ጋር ፡ ነው ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ አትርፈን ፡ እንገዛቸዋለን ፡ ማለታቸው ። አንድም ፡ በትሩፋን ፡ ዘንድ ፡ ጻዕር ፡ ገዓር ፡ ነው ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ሲፈጸም ፡ አወጣችኋለሁ ፡ ብሏቸዋል ፡ ይህ ፡ ከቀረ ፡ መቅረቱ ፡ ነውና ። አንድም ፡ (ወመዋዕለ ፡ ዓመቲነኒ) ፡ ለሁሉ ፡ አድርጎ ፡ ተናግሮታል ፡ ብሎ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖረው ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ነው ። (ወእመሰ ፡ በዝኃ) ፡ ዕልፍም ፡ ቢል ፡ ሰማንያ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ (ወፈድፋዶንሰ) ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ጻዕር ፡ ገዓር ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ዓይን ፡ ይፈዛል ፡ ጆሮ ፡ ይደነግዛል ፡ አፍንጫ ፡ ያነዝዛል ፡ ወገብ ፡

ይያዛልና ። አንድም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ከሚኖረው ፡ ይልቅ ፡ በመከራ ፡ የሚኖረው ፡ ይበዛልና ።

አንድም፡ (ወመዋዕለ ፡ ዓመቲነ) ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ የሚኖረው ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ (ወእመሰ) ፡ ከሰባት ፡ ሺሕም ፡ እልፍ ፡ ቢል ፡ ስምንት ፡ ሺሕ፡ ነው ፡ (ወፈድፋዶንሰ) ፡ ከስምንት ፡ ሺሕ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በጻድቃን ፡ ዘንድ ፡ ጻር ፡ ጋር ፡ ነው ፡ ከስምንት ፡ ሺሕ ፡ በኋላ ፡ መጥቼ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ አሳልፌ ፡ ዋጋችሁን ፡ እሰጣችኋለሁ ፡ ብሏቸዋል ፡ ይህ ፡ የቀረ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መቅረት ፡ ነውና ። አንድም ፡ በኃጥአን ፡ ዘንድ ፡ ጻዕር ፡ ገዓር ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ከገሃነም ፡ መከራ ፡ የሲኦል ፡ መከራ ፡ ይቀላል ፡ ይባላልና ።

እስመ ፡ ኀለፈት ፡ የዋሃት ፡ እምኔነ ፡ ወተገሠፅነ ።

ሕግ ፡ መጠበቅ ፡ አንድም ፡ ቅንነት ፡ ከኛ ፡ ጠፍቷልና ፡ በመከራውም ፡ ተገሥፀናልና ፡ ወፈድፋዶንሰ ፡ ላለው ፡ አንድም ፡ ሕግ ፡ መጠበቅ ፡ ከኛ ፡ ጠፍቷልና ፡ በመከራው ፡ ተገሠፅን ።

፲፩ ፡ መኑ ፡ የአምር ፡ ኃይለ፡ መቅሠፍትከ

መከራ ፡ ባታመጣብን ፡ መቅሠፍትህን ፡ የምታመጣበት ፡ ኃይልህን ፡ ማን ፡ ባወቀው ፡ ነበር ።

እምግርማ ፡ መዓትከ ፡ ኀልቁ ።

ከመዓትህ ፡ መፍራት ፡ የተነሣ ፡ ማለት ፡ መዓትህን ፡ ከመግለዕህ ፡ የተነሣ ፡ ተፈጸሙ ።

፲፪ ፡ ከመዝ ፡ አርኢ ፡ የማነከ ።

ኃልቁ ፡ ብዬ ፡ እንደ ፡ ተናገርሁ ፡ ሥልጣንህን ፡ ግለጽ ።

ለምሁራነ ፡ ልብ ፡ በጥበብ ።

ጥበብን ፡ አንድም ፡ ሕግን ፡ ለምናውቅ ፡ ለኛ ።

፲፫ ፡ ተመየጥ ፡ እግዚኦ ፡ እስከ ፡ ማዕዜኑ

አቤቱ ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ ተመለስ ፡ እንጂ ፡ የማትመለስ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ።

ወተናበብ ፡ በእንተ ፡ አግብርቲከ ።

ስለ ፡ ባሮችህ ፡ ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናገር ፡ ስጠኝ ፡ ፍጃታ ፡ ማለት ፡ አይደለም ፡ የግብር ፡ ሙግት ፡ ነው፡ ፍረድ ፡ ሲል ፡ ነው ።

፲፬ ፡ እስመ ፡ ጸገብነ ፡ በጽባሕ፡ምሕረተከ

በሰባ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ንጋት ፡ ደስ፡ የሚያሰኝ ፡ ቸርነትህን ፡ አግኝተናልና ፡ ደስ ፡ አለን ።

ተፈሣሕነ ፡ ወተሐሠይነ ፡ በኵሉ ፡ መዋዕሊነ ።

ባለ ፡ ዘመናችን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ አለን ።

፲፭ ፡ ወተፈሣሕነ ፡ ህየንተ ፡ መዋዕል ፡ ዘአሕመምከነ ።

ሰባ ፡ ዘመን ፡ መከራ ፡ ስለ ፡ ተቀበልነ ፡ (ዘመን) ፡ ፈንታ ።

መሀየንተ ፡ ዓመት ፡ እንተ ፡ ርኢናሃ ፡ ለ እ ኪ ት ።

ሰባ ፡ ዘመን ፡ የመከራዋን ፡ ፅናት ፡ ስለ ፡ አየነ ፡ (ዘመን) ፈንታ

፲፯ ፡ ርኢ ፡ ላዕለ ፡ አግብርቲከ ፡ ወላዕለ ተግባርከ ፡ እግዚእ ።

አቤቱ ፡ ፍጥረቶችህ ፡ አገልጋዮ ችህ ፡ የሚሆኑ ፡ አብርሃም ፡ ይስ ሐቅ ፡ ያዕቆብን ፡ እይ ፡ ተመል ከት ፡ ተግባርንና ፡ አግብርትን ፡ ላዕለንና ፡ ላዕለን ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ አድርገህ ።

ወምርሆሙ ፡ ለደቂቆሙ ።

እንዲህ ፡ ዓይተህ ፡ ተመልከተህ ፡ ልጆቻቸው ፡ ትሩፋንን ፡ ከባቢ ሎን ፡ መርተህ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም፡ አውጣቸው ።

፲፯ ፡ ለይኩን ፡ ብርሃኑ ፡ ለእግዚአብሔር እ ም ላ ክ ነ ፡ ላ ዕ ሌ ነ ።

የ እ ግ ዚ አ ብሔር ፡ ረድኤቱ ፡ ይደረ ግልን ።

ወይሠርኅ ፡ ለነ ፡ ተግባረ ፡ እደዊነ ።

እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የእ ጃችን ፡ ሥራ ፡ የቀና ፡ ይሆናል ፡ ማለት ፡ የተከልነው ፡ ይጸድቃል ፡ የዘራነው ፡ ይበቅላል ፡ አንድም ፡ የፈጣሪያችን ፡ ሚጠቱ ፡ ይደረግል ን ፡ (ወይሠርኅ) ፡ እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቀኝ ፡ እጃችን ፡ መወ ርወር ፡ በግራ ፡ እጃችን ፡ መመከ ት ፡ ይሆንልናል ።

አንድም ፡ (እስመ ፡ ጸገብነ) ፡ ባም ስት ፡ ሺሕ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘ መን ፡ እንደ ፡ ንጋት ፡ ደስ ፡ የሚ ያሰኝ ፡ ካንተ ፡ የሚገኝ ፡ ልጅነት ፡ አግኝተን ፡ ደስ ፡ ብሎናልና ፡ (ተፈ ሣሕነ፡ ወተሐሠይነ ፡ በኵሉ ፡ መዋ ዕሊነ) ፡ ባለ ፡ ዘመናችን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ አለን ፡ (ወተፈሣ ሕነ ፡ ህየንተ ፡ መዋዕል ፡ ዘአሕ መምከነ) አምስት ፡ ሺህ ፡ አም ስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ መከራ ፡ ነ ፍስ ፡ ስለ ፡ ተቀበልነ ፡ ፈንታ ፡ ደስ ፡ አለን ፡ ወህየንተ ፡ ዓመት ፡ እንተ ፡ ርኢናሃ ፡ ለእኪት) ፡ የመከ ራ ፡ ነፍስ ፡ ፅናቷን ፡ ስለ ፡ አየንበት፡ ዘመን ፡ ፋንታ ፡ ደስ ፡ አለን ፡ (ርኢ ፡ ላዕለ ፡ አግብርቲከ ፡ ወላዕለ ፡ ተግ ባርከ ፡ እግዚኦ) ፡ ተግባር ፡ ከፍጥ ረቶችህ ፡ የሚሆኑ አዳምና ፡ ሔ ዋንን ፡ አግብርቲከ ፡ ነቢያት ፡ ካህ ናትን ፡ እይ ፡ ተመልከት ፡ (ወም ርሆሙ ፡ ለደቂቆሙ) ፡ እንዲህ ፡ አይተህ ፡ ተመልክተህ ፡ ልጆቻ ቸው ፡ ምዕመናንን ፡ ከሲኦል ፡ መርተህ ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ አውጣ ቸው ፡ (ለይኩን ፡ ብርሃኑ ፡ ለእግ ዚ አ ብ ሔ ር፡ አምላክነ ፡ ላዕሌነ) ፡ የፈጣሪያችን ፡ የ እ ግ ዚ አ ብሔር ፡ አ ብ ፡ ብ ር ሃ ኑ ፡ ወ ል ድ ፡ በሥጋ ፡ ይሁን ፡ (ወይሠርኅ ፡ ለነ ፡ ተግባረ ፡ እደዊነ) ፡ እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡

ሆነ ፡ ትንቢተ ፡ ቃልነ) ፡ የተናገር ነው ፡ ትንቢት ፡ ያስተማርነው ፡ ትምህርት ፡ እውነት ፡ ይሆናል ፡ አንድም ፡ (ለይኩን ፡ ብርሃኑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ ላዕሌነ) ፡ የፈጣሪያችን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ብርሃኑ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በኛ ፡ ይደር ፡ (ወይሠርጎ ፡ ለነ ፡ ተግባረ ፡ እደዊነ) ፡ እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ፡ ጸሎተ ፡ ቃልነ ፡ መሥዋዕተ ፡ እደዊነ ፡ የጸለይነው ፡ ጸሎት ፡ የሠዋ ነው ፡ መሥዋዕት ፡ ያርጋል ።

## መዝሙር ፡ ፺ ።

፩ ፤ ዘየኀድር ፡ በረድኤተ ፡ ልዑል ።

ስለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ፡ የምዕመናንም ፡ ነገር ፡ አለበት ፡ በልዑል ፡ እግዚአብሐር ፡ ረድኤት ፡ ተጠብቆ ፡ የሚኖር ፡ ሕዝቅያስ ፡ አንድም ፡ ባሕታዊ ፡

ወይነብር ፡ ውስተ ፡ ጽላሎቱ ፡ ለአምላከ ፡ ሰማይ ።

ሰማይን ፡ በፈጠረ ፡ በእግዚአብሔር ጽላሎተ ፡ ረድኤት ፡ ተጠብቆ ፡ የሚኖር ፡ ሕዝቅያስ ፡ አንድም ፡ ተጠብቆ ፡ የሚኖር ፡ ባሕታዊ ።

፪ ፤ ይብሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስካይየ አንተ ።

እግዚአብሔርን ፡ አምባ፡ መጸጊያዬ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ይለዋል ።

አምላኪየ ፡ ወረዳኢየ ፡ ወእትዌከል፡ቦቱ።

ፈጣሪዬ ፡ ነው ፡ ረዳቴ ፡ ነው ፡ እኔም ፡ ይረዳኛል ፡ ብዬ ፡ አምንበታለሁ ።

፫ ፤ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይባልሐኒ ፡ እመሥገርት ፡ ነዓዊት ።

እሱ ፡ ከከባቢ ፡ ወፅመድ ፡ ያድነኛልና ፡ አንድም ፡ ከሚከብቡኝ ፡ ከነ ሰናክሬም ፡ አንድም ፡ ከመከራው ፡ አንድም ፡ ከፀብዓ ፡ ሰይጣን ፡ ያድነኛልና ።

ወእምነገር ፡ መደንግፅ ።

ከሚያስደነግፅ ፡ ከሰናክሬም ፡ ነገር ፡ አንድም ፡ ከሰይጣን ፡ ጦር ፡ ያድነኛልና ፡ መደንግፅ ፡ ቃል ፡ የሀውክ ፡ ልበ ፡ ብእሲ ፡ እንዲል

ምሳ ፡ ፲፪ ፡ ፳፭ ።

፬ ፤ ይጼልለከ ፡ በገበዋቲሁ ።

ሕዝቅያስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አመንህ ፡ አበጀህ ፡ በጽላሎተ ፡ ረድኤቱ ፡ ከመከራው ፡ ይሠውርሃል ።

ወትትዌከል ፡ በታሕተ ፡ ክነፊሁ ።

በክንፈ ፡ ረድኤቱ ፡ ተጠብቀህ ፡ ትኖራለህ ።

ጽድቅ ፡ በወልታ ፡ የዐውደከ ።

ቸርነት ፡ እንደ ፡ ጋሻ ፡ ሁኖ ፡ ይጠብቅሃል ።

፫ ፤ ወኢትፈርህ ፡ እምግርማ ፡ ሌሊት ።
ኢትፍራህም ፡ ይላል ፡ ከሌሊት ፡ መፈራት ፡ ማለት ፡ ከሰይጣን ፡ አንድም ፡ ከፀብዓ ፡ አጋንንት ፡ የተነሣ ፡ አትፈራም ፡ አትፍራ ።

እምሐጽ ፡ ዘይሠርር ፡ በመዓልት ።
በመዓልት ፡ ከሚወረወር ፡ ጦር ፡ ማለት ፡ ከቀን ፡ ወራሪ ፡ ከፀብዓ ፡ አጋንንት ፡ አትፈራም ፡ አትፍራህ።

፮ ፤ እምግብር ፡ ዘየሐውር ፡ በጽልመት
በጨለማ ፡ ከሚሄድ ፡ ማለት ፡ ከሌሊት ፡ ሰባሪ ፡ አንድም ፡ ከፀብዓ ፡ አጋንንት ፡ አትፈራም ፡ አትፍራ ።

እምድድቅ ፡ ወእምጋኔን ፡ ቀትር ።
ከአደጋ ፡ ነገር ፡ ከሰናክሬም ፡ የተነሣ ፡ አትፈራም ፡ አትፍራ ።

ሐተታ ፡ ሰናክሬም ፡ ከለኪሶን ፡ የሰፈረ ፡ በቀትር ፡ ነውና ፡ ጋኔን ፡ ቀትር ፡ አለው ፡ አንድም ፡ ከፀብአ ፡ አጋንንት ፡ ከዲያብሎስ ፡ አትፈራም ፡ ሰው ፡ ሥራውን ፡ ሲሠራ ፡ ውሎ ፡ ቀትር ፡ ሲሆን ፡ ፀሐይ ፡ ናላውን ፡ ባቃጠለው ፡ ጊዜ ፡ አእምሮው ፡ ይፈዛል ፤ አጋንንት ፡ ድል ፡ ይነሡታልና ፡ አንድም ፡ ዲያብሎስ ፡ አዳምንና ፡ ሔዋንን ፡ ድል ፡ የነሣው ፡ (ያሳተው)፡ በቀትር፡ነውና።

፯ ፤ ይወድቁ ፡ በገቦከ ፡ ዐሠርቱ ፡ ምዕት ።
በግራህ ፡ በወረወርህ ፡ ጊዜ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ይወድቃሉ ።

እዕላፍ ፡ በየማንከ ፡ ወኀቤከሰ፡ኢይቀርቡ
በቀኝህ ፡ በወረወርህ ፡ ጊዜ ፡ እልፍ ፡ ሰዎች ፡ ይወድቃሉ ፡ ወዳንተ ፡ ግን ፡ አይቀርቡም ። አንድም ፡ (ይወድቁ ፡ በገቦከ ፡ ፲፻) ፡ በግራህ ፡ ባማተብህ ፡ ጊዜ ፡ ሺሕ ፡ አጋንንት ፡ ድል ፡ ይነሣሉ ፡ (እዕላፍ ፡ በየማንከ) ፡ በቀኝህም ፡ ባማተብህ ፡ ጊዜ ፡ እልፍ ፡ አጋንንት ፡ ድል ፡ ይነሣሉ ፡ (ወኀቤከሰ) ፡ ወዳንተ ፡ግን ፡ አይቀርቡም ።

፰ ፤ ወባሕቱ ፡ ትሬኢ ፡ በአዕይንቲከ ።
ነገር ፡ ግን ፡ ሲጠፉ ፡ ባይንህ ፡ ታያለህ ፡ እንጂ ፡ አይቀርቡም ።

ወትሬኢ ፡ ፍዳሆሙ ፡ ለኃጥአን ።
እለሰናክሬም ፡ አንድም፡ አጋንንት ፡ ፍዳቸውን ፡ ሲቀበሉ ፡ ታያለህ ።

፱ ፤ እስመ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ ተስፋየ ፡ መዝ ፡ ፸፩ ።
አቤቱ ፡ አንተ ፡ አለኝታዬ ፡ ነህና ፡ አምን ፡ ይደረግልኛል ።

ልዑለ ፡ ረሰይከ ፡ ፀወንከ ።
እንዲህ ፡ አልህ ፡ ሕዝቅያስ ፡ አንድም ፡ ባሕታዊ ፡ አበጀህ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ አምባ ፡ መፀግያ ፡ አደረግህ ።

፲ ፤ ወኢይቀርብ ፡ እኩይ ፡ ኀቤከ ።
ሰናክሬም ፡ አንድም ፡ ዲያብሎስ ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ አይቀርብም ።

ወኢይበውእ ፡ መቅሠፍት ፡ ቤተከ ።

መቅሠፍት ፡ ወደ ፡ ቤትህ ፡ አይገባም ፡ አንድም ፡ በወገኖችህ ፡ አይታዘዝም ፡ አንድም ፡ ሰናክሬም ፡ አንድም ፡ ፀብዓ ፡ አጋንንት ፡ ወደ፡ ቤትህ ፡ አይገባም ።

፲፩ ፡ እስመ ፡ ለመላእክቲሁ ፡ ይኤዝዞሙ፡ በእንቲአከ ።

ስለ ፡ አንተ ፡ መላእክትን ፡ ያዝዛቸዋልና ፡

ከመ ፡ ይዕቀቡከ ፡ በኵሉ ፡ ፍናዊከ ። ዘፀ ፡ ፳፫ ፡ ፳ ።

በሥራህ ፡ ሁሉ ፡ ይጠብቁህ ፡ ዘንድ ፡ ማቴ ፡ ፬ ፡ ፮ ።

፲፪ ፡ ወበእደዊሆሙ ፡ ያነሥኡከ ።

ያንሥኡከም ፡ ይላል ፡ በእጃቸው ፡ ያነሡሃል ፡ አንድም ፡ ያነሡህ ፡ ዘንድ ፡

ከመ ፡ ኢትትዐቀፍ ፡ በዕብን ፡ እግርከ ።

ኢይትዓቀፍ ፡ በዕብን ፡ እግርከ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እግርህ ፡ በደንጊያ ፡ እንዳይመታ፡ አንድም፡ (ከመ ፡ ኢትትዓቀፍ ፡ በዕብን ፡ እግረከ) ፡ እግርህን ፡ በደንግያ ፡ እንዳትመታ ፤ ቅዱሳን ፡ ሲበቁ ፡ ባንበሳ ፡ በዘንዶ ፡ ይቀመጣሉና ። ሉቃ ፡ ፬ ፡ ፲፩ ።

፲፫ ፡ ላዕለ ፡ ተኵላ ፡ ወከይሲ ፡ ትጼዓን ።

ላዕለ ፡ ተኩላ ፡ በሰናክሬም ፡ ላይ ፡ ወከይሲ ፡ በመሮዳህ ፡ ላይ ፡ ትሠለጥናለህ ።

ወትከይድ ፡ አንበሳ፡ወከይሴ ፡ ሉቃ፡፲፡፲፱

ተኵላ ፡ ያለውን ፡ አንበሳ ፡ ከይሲ ፡ ያለውን ፡ ከይሲ ፡ ብሎ ፡ ደገመው ።

፲፬ ፡ እስመ ፡ ብየ ፡ ተወከለ ፡ አድኅኖ ።

በኔ ፡ አምኗልና ፡ አድነዋለሁ ።

ወእከድኖ ፡ እስመ ፡ አእመረ ፡ ስምየ ፡

ስሜን ፡ መጥራት ፡ ወዷልና ፡ ከመከራው ፡ እሰውረዋለሁ ።

፲፭ ፡ ይጼውዓኒ ፡ ወእሰጠዎ ።

ይለምነኛል ፡ እኔም ፡ ልመናውን ፡ እቀበለዋለሁ ፡ የለመነኝን ፡ አደርግለታለሁ ።

ሀሎኩ፡ ምስሌሁ ፡ አመ ፡ ምንዳቤሁ ። ኤር ፡ ፴ ፡ ፲፩ ።

ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ነበርሁ ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህም ፡ (እሺሉ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ በመከራው ፡ ጊዜ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ እኖራለሁ ።

አድኅኖ ፡ ወእሴብሖ ።

ከመከራው ፡ አድኜ ፡ አከብረዋለሁ፡ አንድም ፡ (አድኅኖ) ፡ ከመከራው ፡ አድነዋለሁ ፡ (ወእሴባሕ ፡ ቦቱ) ፡ ይላል ፡ እመሰገንበታለሁ ፡ አንድም ፡ እሱን ፡ አድኜ ፡ ክብሬን ፡ እገልጽበታለሁ ።

፲፮ ፡ ለነዋኅ ፡ መዋዕል ፡ አጸግቦ ።

ነዋህ ፡ መዋዕለ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ረጅም ፡ ወራት ፡ ሰፊ ፡ ዘመናት ፡ ሰጥቼ ፡ ደስ ፡ አሰኘዋለሁ ።

ወአርእዮ ፡ አድኅኖትየ ።
ትድግናዬን ፡ እገልጽለታለሁ ፡ መዝ ፡
፺፯ ፡ ፪ ። ኢሳ ፡ ፴፰ ፡ ፰ ።
ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ
ቅዱስ ፡ ለዓለም ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፡
ለአብና ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡
ቅዱስም ፡ ክብርና ፡ ምስጋና ፡ ይግ
ባቸው ። ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡
ምፅአት ፡ ድረስ ፡ ከምፅአትም ፡
በኋላ ፡ ለዘላለሙ ።
አሜን ።
በእውነት ፡ እንበል ፡ ሐሰት ።

## መዝሙር ፡ ፺፩ ።

፩ ፡ ይኄይስ ፡ ተአምኖ ፡ በእግዚአብሔር
ስለ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ተናግሮታል ፡ እን
ደ ፡ ሰናክሬም ፡ በፈረስ ፡ በሠረገላ ፡
ከመታመን ፡ በእግዚአብሔር ፡ መ
ታመን ፡ (ማመን) ፡ ይበልጣል ፡
(ይሻላል) ።

ወዘምሮ ፡ ለስምከ ፡ ልዑል ።
ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ስምህን ፡
ማመስገን ፡ ለስምህ ፡ ምስጋና ፡ ማቅ
ረብ ፡ ይበልጣል ፡ (ይሻላል) ።

አንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡
ስምህን ፡ ማመስገን ፡ ይበልጣል ፡
(ይሻላል) ።

፪ ፡ ወነጊር ፡ በጽባሕ ፡ ምሕረተከ ።
ቸርነትህንም ፡ በቀን ፡ መናገር ፡
ይበልጣል ።

ወጽድቀከኒ ፡ በሌሊት ።
ምሕረተከ ፡ ወጽድቀከ ፡ ቸርነትህ
ንም ፡ በመዓልት ፡ በሌሊት ፡ መና
ገር ፡ ይበልጣል ።

፫ ፡ በዘዐሠርቱ ፡ አውታሪሁ ፡ መዝሙረ
ማኅሌት ፡ ወመሰንቆ ።
ዐሥር ፡ አውታር ፡ ያለው ፡ የም
ስጋና ፡ በገና ፡ እየደረደሩ ፡ መሰን
ንቆ ፡ እየመቱ ፡ አንድም ፡ ዐሥር ፡
ሕዋሳት ፡ ባለው ፡ ሰውነት ፡ በሃ
ይማኖት ፡ ፀንቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
መገዛት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማመ
ስገን ፡ ይበልጣል ።

፬ ፡ እስመ ፡ አስተፍሥሕከኒ ፡ እግዚአ ፡
በምግባሪከ ።
አቤቱ ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ሥራ ፡
ሠርተህ ፡ ማለት ፡ ሰናክሬምን ፡
ገድለህ ፡ ደስ ፡ አሰኘተኸኛልና ፡
ይኄይስ ፡ አንድም ፡ እንዲህ ፡ ነውና ፡

ወእትሐሠይ ፡ በግብረ ፡ እደዊከ ።
ከእንግዲህ ፡ ወዲህም ፡ በእጅህ ፡
በቃልህ ፡ በምትሠራልኝ ፡ ሥራ ፡
ማለት ፡ ድህነተ ፡ ደዌን ፡ አድርገህ ፡
ደስ ፡ ታሰኘኛለህ ።

፭ ፡ ጥቀ ፡ ዐቢይ ፡ ግብርከ ፡ እግዚኦ ።
፻፫ ፡ ፳፬ ።

አቤቱ ፡ ሥራህ ፡ እጅግ ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ ረቂቅ ፡ ነው ።

ወፈድፋደ ፡ ዕሙቅ ፡ ኅሊናከ ።

ባሕርይህ ፡ አንድም ፡ ፍርድህ ፡ ፈጽሞ ፡ ጥልቅ ፡ ነው ።

፮ ፡ ብእሲ ፡ አብድ ፡ ኢየአምር ።

ሰነፍ ፡ ሰናክሬም ፡ አንድም ፡ ማናቸውም ፡ ሰነፍ ፡ ሥራህ ፡ ረቂቅ ፡ ባሕርይህ ፡ ፍርድህ ፡ ጥልቅ ፡ መሆኑን ፡ አያውቅም ።

ወዘአልቦ ፡ ልብ ፡ ኢይሌብዎ ፡ ለዝንቱ።

ወዘአልቦ ፡ ልብ ፡ ለማለት ፡ ደገመው ፡ ልብ ፡ የሌለው ፡ ሰናክሬም ፡ አንድም ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ አያስተውለውም ።

፯ ፡ ሶበ ፡ ይበቍሉ ፡ ኃጥኣን ፡ ከመ ፡ ሣዕር

እለ ፡ ሰናክሬም ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ በዝተው ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ፡

ወይሠርፁ ፡ ኵሎሙ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ ።

ዓመፅን ፡ የሚሠሩ ፡ እነሰናክሬም ፡ በዝተው ፡ ቢነሡ ፡

ከመ ፡ ይሠረዉ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

እንዲህ ፡ በዝተው ፡ ሊቀሩ ፡ አይደለም ፡ ለዘላለም ፡ ተነቃቅለው ፡ ይጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ነው፡ እንጂ ፡

፰ ፡ አንተሰ ፡ ልዑል ፡ ለዓለም ፡ እግዚኦ

አቤቱ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ለዘላለም ፡ የምትኖር ፡ ልዑል ፡ ነህ ፡ አጥፊ ፡ ለጥፋት ፡ የሚልህ ፡ የለም ።

፱ ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ ጸላእትከ ፡ ይትሐጐሉ

እነሆ ፡ ጠላቶችህ ፡ እለሰናክሬም ፡ ይጠፋሉና ፡ አንተሰ ፡ ልዑል ፡

ወይዘረዉ ፡ ኵሎሙ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ ።

ዓመፅን ፡ የሚሠሩ ፡ ሁሉ ፡ ይጠፋሉና ።

፲ ፡ ወይትሌዓል ፡ ቀርንየ ፡ ከመ ፡ ዘአሐዱ ፡ ቀርኑ ።

እኔ ፡ ግን ፡ ከብሬ ፡ ገንኜ ፡ እኖራለሁ ፡ አንድም ፡ የኔ ፡ ግን ፡ ሥልጣኔ ፡ ቀንዱ ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደ፡ ርኤም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላልና፡ ልዑል ፡ ላለው ።

ወይጠልል ፡ በቅብዕ ፡ ሲበትየ ።

በዘይት ፡ ይለመልማል ፡ ማለት ፡ የምበላውን ፡ የምጠጣውን ፡ ሳላጣ ፡ ከልጅነት ፡ እስከ ፡ ሺበት ፡ እደርሳለሁ ፡ አረጃለሁ ።

፲፩ ፡ ወርእየት ፡ ዓይንየ ፡ በጸላእትየ ።
መዝ ፡ ፶፫ ፡ ፯ ።

ዓይኔ ፡ ሠራዊቱ ፡ ጠፍተው ፡ አየች፡ አንድም ፡ ዘኮነ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ ዓይኔ ፡ በሠራዊቱ ፡ የተደረገውን ፡ አየች ።

ወሰምዓት ፡ ዕዝንየ ፡ ዲቤሆሙ ፡ ለእኩያን ፡ እለ ፡ ቆሙ ፡ ላዕሌየ ።

በጸላትነት ፡ በተነሡብኝ ፡ በክፉዎች ፡ ነገሥታቱ ፡ ላይ ፡ የተደረገ

ውንም ፡ ጆሮዬ ፡ ሰማች ፤ ቁም ፡ ላዕሌየ ፡ ወቅትለኒ ፡ እንዲል ፡

፲፪ ፤ ጻድቅሰ ፡ ከመ ፡ በቀልት ፡ ይፈሪ ። ኢዮ ፡ ፬ ፡ ፲፪ ። ፲፫ ፡ ፩ ።

ጻድቅ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ግን ፡ አንድም ፡ ማናቸውም ፡ ጻድቅ ፡ እንደ ፡ ዘንባባ ፡ ያፈራል ፡ ማለት ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ ያገኛል ፡

ወይበዝኅ ፡ ከመ ፡ ዘግባ ፡ ዘሊባኖስ ።

በደጋ ፡ እንደ ፡ ተተከለ ፡ ዘግባ ፡ ይሆናል ፡ ማለት ፡ ያ ፡ ከፍሬ ፡ እንዲደርስ ፡ ብዙ ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ ያገኛል ።

፲፫ ፤ ትኩላን ፡ እሙንቱ ፡ ውስተ ፡ ቤተ እግዚአብሔር ።

እነዚህም ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተተከሉ ፡ ናቸው ፤ አንድም ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ። እንደ ፡ ተተከሉ ፡ እንደ ፡ ዘግባ ፡ እንደ ፡ ዘንባባ ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ብዙ ፡ ፍሬ፡ እንዲያፈራ፡ እነሱም ፡ ብዙ ፡ ፀጋ ፡ ክብር ፡ ያገኛሉ ።

ወይበቍሉ ፡ ውስተ ፡ ዐጸዱ ፡ ለአምላክነ።

በፈጣሪያችን ፡ ቦታ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንደ ፡ በቀሉ ፡ እንደ ፡ ዘግባ ፡ እንደ ፡ ዘንባባ ፡ ናቸው ።

፲፬ ፤ ውእተ ፡ አሚረ ፡ ይበዝኁ ፡ በርሥዓን ፡ ጥሉል ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ ማለት ፡ በጎ ፡ ንጉሥ ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ ሕፃን ፡ አረጋዊ ፡ በበጎ ፡ ዕርግና ፡ ያረጃሉ ፡ ማለት ፡ ሕፃኑ ፡ ወተት ፡ ፍትፍት ፡ ሳያጣ ፡ አረጋዊው ፡ መውጣት ፡ መውረድ፡ ሳይኖርበት ፡ ይኖራል ።

ወይከውኑ ፡ ዕሩፋነ ።

ከመከራው ፡ ያርፋሉ ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ ይኖራሉ ።

፲፭ ፤ ወይነግሩ ፡ ከመ ፡ ጻድቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ።

ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይነግራሉ ፡ ያስተምራሉ ፤ አንድም፡ (ይንግሩ) ፡ ያስተምሩ ።

ወአልቦ ፡ ዐመፃ ፡ በኀቤሁ ።

በሱም ፡ ዘንድ ፡ ሐሰት ፡ እንደ ፡ ሌለበት ፡ ይነግራሉ ፡ ያስተምራሉ፡ አንድም ፡ በሱ ፡ ዘንድ ፡ ሐሰት ፡ የለበትም ።

## መዝሙር ፡ ፺፪ ።

፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ ነግሠ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ለብሰ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ እግዚአብሔር ፡ ነግሦ ፡ (የመንግሥቱን ፡ የጌትነቱን ፡ ልብስ ፡ ለበሰ) ፡ ማለት ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ሠራ ።

ለብሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይሎ ፡ ወቀነተ

ስብሐቲሁ ፡ ለብሰ ፡ ወኃይሎ ፡ ቀነተ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ እግዚአ ብሔር ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ሥራ ፡ ኃይልንም ፡ እንደ ፡ ዝናር ፡ ታጠቀ ፡ ማለት ፡ በኃይላቸው ፡ የሚመኩ ፡ ኃያላኑን ፡ አጠፋ ።

ወአጽንዓ፡ለዓለም ፡ ከመ፡ኢታንቀልቅል

ይህችን ፡ ዓለም ፡ አንድም ፡ ኢየሩ ሳሌምን ፡ እንዳትናወጥ ፡ በረድ ኤት ፡ አፀናት ፡ ማለት ፡ ሀገሪቱ ፡ እንዳትፈታ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እን ዳትፈርስ ፡ አደረጋት ።

፪ ፡ ድልው ፡ መንበርከ ፡ እግዚእ ።

ንቡር ፡ ሲል ፡ ነው ፡ አቤቱ ፡ ጌት ነትህ ፡ ለዘላለም ፡ ፀንቶ ፡ ይኖራል ፡ (የኖረ ፡ ነው) ።

እምትካት ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ፡ አንተ ፡ ከመ ።

ትሥሉ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ቅድመ ፡ ዓ ለም ፡ የነበርህ ፡ ዓለምን ፡ አሳል ፈህ ፡ መቼም ፡ መች ፡ ትኖራለህ ፡ የምትኖር ፡ ነህ ። አንድም ፡ ነገሠ ፡ ብዬም ፡ ብናገር ፡ ሥራው ፡ ሐዲስ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ገናስ ፡ ነግሠ ፡ እንዳልልህ ፡ ጌት ነትህ ፡ ለዘላለም ፡ ፀንቶ ፡ የሚኖር ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የነበርህ ፡ ዓለምን፡ አሳልፈህ ፡ መቼም ፡ መች ፡ የምት ኖር ፡ ንጉሥ ፡ ነህ ።

፫ ፡ አልዐሉ ፡ አፍላግ ፡ እግዚእ ፡ አልዐሉ አፍላግ ፡ ቃላቲሆሙ ።

አቤቱ ፡ አፍላግ ፡ ቃላቸውን ፡ ፈጽ መው ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጉ ። ዕን፡፫፡፲።

እምቃለ ፡ ማያት ፡ ብዙኅ ።

ብዙ ፡ ውኆች ፡ ከመግባታቸው ፡ የተነሣ ።

፬ ፡ መንክር ፡ ተላህያ ፡ ለባሕር ።

የባሕር ፡ ጨዋታዋ ፡ ድንቅ ፡ ነው፡ ኃይለኛ ፡ ነፋስ ፡ የገሠፃት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ማዕበል ፡ ሞገዱ ፡ ተራራ ፡ ያህል ፡ ሆኖ ፡ ሲነሣ ፡ ያስደነግ ጣል ፡ መጠነኛ ፡ ነፋስ ፡ ሲነካት ፡ ግን ፡ ወለል ፡ ወለል ፡ እያለች ፡ ስትሄድ ፡ ደስ ፡ ታሰኛለችና ፡ አን ድም ፡ እንደ ፡ ፈረሰኛ ፡ ሁኖ ፡ ሲ ነሣ ፡ ደስ ፡ ያሰኛልና ።

መንክርሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ በአርያም ።

ድንቅስ ፡ በለኝ ፡ እስከ ፡ ዝየ ፡ ብጽ ሒ ፡ ብሎ ፡ የወሰነ ፡ በአርያሙ ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ።

አንድም ፡ (አልዓሉ ፡ አፍላግ) ፡ (አለዓሉ ፡ ቃላቲሆሙ) ፡ አቤቱ ፡ እስራኤል ፡ ቃላቸውን ፡ ለምስጋና፡ ፈጽመው ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጉ ፡ (እምቃለ ፡ ማያት) ፡ ከነቢያት ፡ ትንቢት ፡ ከካህናት ፡ ትምህርት ፡ የተነሣ ፡ (መንክር) ፡ የቤተ ፡ እስ ራኤል ፡ ሥርዓቷ ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ (መንክርሰ) ፡ ድንቅስ ፡ በለኝ ፡

ዘይሜህሮሙ ፡ ለሰብእ ፡ ጥበብ ።

ለሰው ፡ ጥበብን ፡ የሚገልጽ ፡ ሕግን ፡ የሚያስተምር ፡ አያውቅም ፡ አይፈርድምን ፡ ኢየአምር፣ ላለው ።

፲፩ ፡ እግዚአብሔር ፡ የአምር ፡ ኀሊና ፡ ሆሙ ፡ ለጠቢባን ፡ ከመ ፡ ከንቱ ፡ ውእቱ

እንኳን ፡ እሱን ፡ አያውቅም ፡ ልትሉት ፡ እናውቃለን ፡ የሚሉ ፡ የፈላስፎች ፡ ዕውቀት ፡ ከንቱ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ፤ (ታሪክ)፡ እንደ ፡ ሁለት ፡ ፈላስፎች ፡ አንዱ ፡ ፈላስፋ ፡ ሙሴና ፡ መቃብርን ፡ ፈርቶ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ የሞትሁ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አትቅበሩኝ፡ ዕውቀት ፡ ይከፈልባችኋል ፡ ሥጋዬን ፡ ብትበሉት ፡ ግን ፡ ጥበብ ፡ ይገለጽላችኋል ፡ አላቸው ፤ ይሞታል፡ ብለው፡ ቢያዩት፡ የማይሞት ፡ ሆነ ፤ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ እንጠብቀዋለን ፡ ብለው ፡ አርደው ፡ ሥጋውን ፡ ተቀራምተው ፡ በልተውታል ፡ በልው ፡ ዝግኖ ፡ ወሰትዩ ፡ መረቆ ፡ እንዲል ። አንዱ ፡ ሞትን ፡ የሚፈራ ፡ ነው ፡ በፍልስናው ፡ ዕፀ ፡ ሕይወትን ፡ አግኝቶ ፡ ባዲስ ፡ ሸክላ ፡ ዘፍዝፎ ፡ ከመንደር ፡ አጠገብ ፡ ያደረግሁት ፡ እንደሆነ ፡ ለሰው ፡ ይተርፋል ፡ ብሎ ፡ ተመቅኝቶ ፡ ሰው ፡ ከማይደርስበት ፡ እታጠባለሁ ፡ ብሎ ፡ ተሸክሞ ፡ ለመታጠብ ፡ ሲሄድ ፡ ጌታ ፡ ምቀኝነት ፡ አይወድምና ፡ በላዩ ፡ እንዳለ ፡ መልአኩ ፡ ሰበረበት ፡ በእኩሌታው ፡ አካሉ ፡ ፈሰሰበት ፡ እኩሌታው ፡ አካሉ ፡ ሕያው ፡ እኩሌታው ፡ አካሉ ፡ ምውት ፡ ሆኖ ፡ የሚኖር ፡ ሁኗልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፳፪ ።

፲፪ ፡ ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘአንተ ፡ ገሠፅኮ ፡ እግዚእ ።

እስከዚያውም ፡ ድረስ ፡ አቤቱ ፡ አንተ ፡ በመከራ ፡ የሠራኸው ፡ የቀጣኸው ፡ ትሩፍ ፡ አንድም ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ። ኢዮ ፡ ፭ ፡ ፲፯ ።

ወዘመሀርኮ ፡ ሕገከ ።

ሕግን ፡ የገለጽህለት ፡ ያስተማርከው ።

፲፫ ፡ ከመ ፡ ይትገኅሥ ፡ እመዋዕለ ፡ እኩያት ።

መቅሠፍት ፡ ከታዘዘባቸው ፡ ዘመናት ፡ አንድም ፡ እመዋዕለ ፡ እኩያን ፡ እኩያን ፡ ነገሥታት ፡ ከነገሡባቸው ፡ ዘመናት ፡ አንድም ፡ እመዋዕለ ፡ እኩያት ፡ ከክፉዎች ፡ ዘመናት ፡ ይርቅ ፡ ዘንድ ።

እስከ ፡ ይትከረይ ፡ ግብ ፡ ለኃጥእን ።

በባቢሎናውያን ፡ እስኪፈረድባቸው ፡ ድረስ ።

፲፬ ፡ እስመ ፡ ኢይገድፎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሕዝቡ ።

እግዚአብሔር ፡ ዐሥሩን ፡ ነገድ ፡ በመከራው ፡ አይጥላቸውምና ።

ፈጣሪዬ ፡ ነው አንድም ፡ ፈጣሪዬ ፡ አለኝታዬን ፡ የሚያደርግልኝ ፡ ነው ።

፳፫ ፤ ወይፈድዮሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ በከመ ፡ እከዮሙ ።

እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ክፉ ፡ ሥራቸው ፡ መጠን ፡ ፍዳቸውን ፡ ያመጣባቸዋል ።

ወያጠፍዖሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ

ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያጠፋቸዋል ።

## መዝሙር ፡ ፺፬ ።

፩ ፤ ንዑ ፡ ንትፈሣሕ ፡ በእግዚአብሔር ።

ስለ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፡ ይህንም ፡ በዕረፍት ፡ ሳለ ፡ ተናግሮታል ፤ በእግዚአብሔር ፡ አምነን ፡ ደስ ፡ ይበለን ፤ አንድም ፡ ደስ ፡ ይለን ፡ ዘንድ ፡

ወንየብብ ፡ ለአምላክነ ፡ ወመድኃኒነ ።

ድኅነታችንን ፡ ለሚያደርግልን ፡ ፈጣሪያችን ፡ ምስጋና ፡ እናቅርብ ፤ አንድም ፡ እናቀርብ ፡ ዘንድ ።

፪ ፡ ወንብጻሕ ፡ ቅድመ ፡ ገጹ ፡ በአሚን

በሃይማኖት ፡ ፀንተን ፡ ከፊቱ ፡ እንቅረብ ፤ አንድም ፡ በሃይማኖት ፡ ፀንተን ፡ ከፊቱ ፡ እንቀርብ፡ ዘንድ፤

ወበመዝሙር ፡ ንየብብ ፡ ሎቱ ።

በገናውን ፡ እየደረደርን ፡ ለሱ ፡ ምስጋና ፡ እናቅርብ ፤ አንድም ፡ ለሱ ፡ ምስጋና ፡ እናቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ኑ ።

፫ ፤ እስመ ፡ ዐቢይ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክነ ።

ፈጣሪያችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ገናና፡ ነውና ።

ወንጉሥ ፡ ዐቢይ ፡ ውእቱ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ አማልክት ።

አማልክት ፡ ነን ፡ ከሚሉ ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ገናና ፡ ንጉሥ ፡ ነውና።

እስመ ፡ ኢይገድፎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሕዝቡ ።

እግዚአብሔር ፡ ወገኖቹን ፡ ትሩፋንን ፡ በመከራው ፡ አይጥላቸውምና ፡ ንዑ ፡ ንትፈሣሕ ።

፬ ፤ እስመ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ኵሉ፡አጽናፈ ፡ ምድር ። ሚራ ፡ ፲ ፡ ፩ ።

እስመ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ብለህ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ውረድ ፡ አኃዜ ፡ ዓለም ፡ በእራሁ ፡ እንዲለው ፡ ጽንፈ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ በመኻል ፡ እጁ ፡ ተይዟልና ።

አድባር ፡ ነዋኃት ፡ ዚአሁ ፡ ውእቱ ።

ረጃጅሙም ፡ ተራሮች ፡ የሱ ፡ ገንዘቦች ፡ ናቸው ፤ ኢሳ ፡ ፴፱ ፡ ፲፮ ።

፭ ፤ እስመ ፡ እንቲኣሁ ፡ ይእቲ ፡ ባሕር ፡ ወውእቱ ፡ ፈጠራ ።

ባሕር ፡ የሱ ፡ ገንዘብ ፡ ናትና ፡ እሱም ፡ ፈጥሯታልና ።

ወለየብስኒ ፡ እደዊሁ ፡ ገብራ ።

የብስንም ፡ ሥልጣኑ ፡ ፈጥሯታልና።

፮ ፤ ንዑ ፡ ንስግድ ፡ ወንግነይ ፡ ሎቱ ።

እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ነውና ፡ ኑ ፡ እን ስገድለት ፡ እንገዛለት ፡ አንድም ፡ እንሰግድለት ፡ እንገዛለት ፡ ዘንድ ፡ ኑ ።

ወንብኪ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘወእቱ ፡ ፈጠረነ ።

በፈጠረን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ኑ ፡ እናልቅስ ፡ አንድም ፡ እናለቅስ ፡ ዘንድ ፡ ኑ ፡ ማልቀስ ፡ በወለደው ፡ በፈጠረው ፡ ነውና ፡ ኢሳ ፡ ፲፫ ፡ ፮ ።

፯ ፤ እስመ ፡ ውእቱ ፡ አምላክነ ።

እሱ ፡ ፈጣሪያችን ፡ ነውና ።

ንሕነሰ ፡ ሕዝቡ ፡ አባግዓ ፡ መርዔቱ ።

የጥንተ ፡ ተገዥዎች ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ወገኖቹ ፡ ነን ።

፰ ፤ ዮም ፡ እመ ፡ ሰማዕክሙ ፡ ቃሎ ።

ምድረ ፡ ርስት ፡ ትገባላችሁ ፡ የሚ ል ፡ በሰማችሁ ፡ ጊዜ ።

ኢታጽንዑ ፡ ልበክሙ ።

አይችልም ፡ አያገባንም ፡ በማለት ፡ ልቡናችሁን ፡ አታፅኑ ፡ አንድም ፡ (ዮም) ፡ ትንሣኤ ፡ ዕርገት ፡ በአት ፡ ዕረፍት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እንዳለ ፡ ቢነግሯችሁ ፡ (ኢታፅንዑ) የለም ፡ በማለት ፡ ልቡናችሁን ፡ አታፅኑት ።

ከመ ፡ እመ ፡ እምረርዎ ፡ በገዳም ።

በገዳም ፡ ባሳዘኑት ፡ ጊዜ ፡ እንዳሳ ዘኑት ፡ ኢታፅንዑ ፡ ልበክሙ ። አ ንድም ፡ በገዳም ፡ ባሳዘኑት ፡ ጊዜ ፡ እንዳሳዘናቸው ፡ አሳዝናችሁት ፡ እ ንዳያሳዝናችሁ ፡ ልቡናችሁን ፡ አታ ፅኑ ።

ወከመ ፡ እመ ፡ አመከርዎ ።

አምረርዎ ፡ በገዳም ፡ አመከርዎ ፡ በገዳም ፡ ነው ፤ በገዳም ፡ በተፈታተ ኑት ፡ ቀን ፡ ባሳዘኑት ፡ ጊዜ ፡ እንዳ ሳዘናቸው ፡ እንዳያሳዝናችሁ ፡ እን ዳሳዘኑት ፡ እንዳታሳዝኑት ፡ እንዳ ፀኑ ፡ አታፅኑ ።

፱ ፤ ዘአመከሩኒ ፡ አበዊክሙ ።

የፈተኑኝ ፡ አባቶቻችሁ ፡ ናቸው ። ፈተኑኒ ፡ ማንሻ ፡ አንድም ፡ የፈ ተኑኝ ፡ አባቶቻችሁ ።

ፈተኑኒ ፡ ወርእዩ ፡ ምግባርየ ።

ፈተኑኝ ፤ ፈተኑኝና ፡ ሥራዬን ፡ አወቁ ። ዘፀ ፡ ፲፯ ፡ ፯ ። ኢሳ ፡ ፳፫ ፡ ፲ ።

፲ ፤ አርብዓ ፡ ዓመተ ፡ ተቈጣዕክዎሙ ፡ ለይእቲ ፡ ትውልድ ።

ተቈጣዕክዎሙ ፡ ካለ ፡ ለእሙንቱ ፡ ለይእቲ ፡ ካለ ፡ ተቈጣዕክዋ ፡ ቢል ፡ በቀና ፡ ነበር ፤ ልማደ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ። ያርባውን ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ያርባ ፡ ዘመን ፡ መንገድ ፡ ይሁን ባቸው ፡ ብዬ ፡ ፈረድሁባቸው ፤

ደ ፡ ነገሠ ፡ ለአሕዛብ ፡ ንገሯቸው ፡

ወአጽንዓ፡ለዓለም፡ከመ፡ኢታንቀልቅል

ኢየሩሳሌም ፡ እንዳትናወጽ ፡ በረ ድኤት ፡ አፀናት ።

ወይኬንኖሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ በርትዕ ።

አሕዛብን ፡ በውነት ፡ ፈርዶ ፡ ያጠ ፋቸዋል ።

፲፩ ፤ ይትፌሥሓ ፡ ሰማያት ፡ ወትትሐ ሠይ ፡ ምድር ።

ሰማይና ፡ ምድር ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ ማለት ፡ ሰማይ ፡ ዝና ም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ ይሰ ጣል ፤ ምድርም ፡ የተከሉባትን ፡ ታጸድቃለች ፡ የዘሩባትን ፡ ታበቅ ላለች ፤ አንድም ፡ ሰማያት ፡ መ ላእክት ፡ ልውላን ፡ (ምድር) ፡ ደ ቂቀ ፡ አዳም ፡ ትሑታን ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፤ ልዑላን ፡ ትሑ ታን ፡ በሁሉ ፡ አሉ ።

ወትትከወስ ፡ ባሕር ፡ በምልዓ ።

ባቢሎን ፡ ግን ፡ መላዋ ፡ ትደረጻ ለች ፡ ኢሳ ፡ ፲፬ ፡ ፺ ።

፲፪ ፤ ትትሐሠይ ፡ ገዳም ፡ ወኵሉ ፡ ዘውስቴታ ።

ይህቺ ፡ ዓለም ፡ በውስጧም ፡ የሚ ኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፤ አን ድም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በውስጧም ፡ የሚኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ ሰባ ፡ ዘመን ፡ ፈት ፡ ሁናለችና ፡ ገዳም ፡ አላት ፡ ኢየሩሳሌምን ።

ውእተ ፡ አሚረ ፡ ይትፌሥሑ ፡ ኵሉ ፡ ዕፀወ ፡ ገዳም ።

ጌታ ፡ ዝናም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡ ለመ ከር ፡ በሰጠ ፡ ጊዜ ፡ በበረኃ ፡ ያሉ ፡ ዕፀዋት ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ይለመልማሉ ፡ ያብባሉ ፡ ያፈራሉ ፡ አንድም ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ከባቢሎን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጥተው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖ ሩ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል።

እምቅድመ፡ገጹ፡ለእግዚአብሔር፡እስመ ይመጽእ ። ኢሳ ፡ ፴፭ ፡ ፩ ። ፵፬ ፡ ፲፫ ።

የእግዚአብሔር ፡ ገጽ ፡ ምሕረት ፡ ከመገለጽ ፡ የተነሣ ፡ ይመጽእ ፡ ይመጣልና ።

፲፫ ፤ ይመጽእ ፡ ወይኴንና ፡ ለምድር ።

መጥቶስ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ፡ ትለኝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለምድር ፡ ይፈርድላ ታል ፡ በምድር ፡ ይፈርድባታል ፤ ሁለት ፡ አርእስት ፡ ተናገረ ፡ ለሁለ ቱም ፡ ያመጣል ።

ወይኴንና ፡ ለዓለም ፡ በጽድቅ ።

ለኢየሩሳሌም ፡ በውነት ፡ ይፈርድ ላታልና ፡ ይፈርድላታል ፡ ላለው ፡

ወለአሕዛብኒ ፡ በርትዕ ።

በባቢሎንም ፡ በውነት ፡ ይፈርድባታ ልና ፡ ይፈርድባታል ፡ ላለው ፤ አን ድም ፡ ከአካል ፡ ጣለው ፤ ለሕዝቡ ፡ ይፈርድላቸዋልና ፡ በአሕዛብ ፡ ግን ፡ ይፈርድባቸዋልና ።